# ስኬቶቻችን በዘፈቀደ የመጡ ሳይሆኑ ታቅዶ በመሰራቱ ነው

**አባ መላኩ** 01-02-17

አገራችን ባለፉት አስራ አራት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይ ያለው ባለሁለት አሃዝ የኤኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ ከመቻሏም ባሻገር ለውጡ በሁሉም መስኮች በመሆኑ ይብዛም ነስም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ ነው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የሚተዳደርበትን የግብርና ዘርፍ መሰረት ያደረገ በመሆኑ ዕድገቱ የሁሉንም አርሶ አደሮች ህይወት ዳሷል ማለት ይቻላል። በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2008ና 2009 የምዕራባዊያኖች ኤኮኖሚ በቀውስ በተመታ ጊዜ የበርካታ የታዳጊ አገሮች በተለይ በተፈጥሮ ሃብት ላይ የተንጠለጠለ ኤኮኖሚ ያላቸው የአፍሪካ አገሮች ችግር ላይ ወድቀው ነበር። ይሁንና የኢትዮጵያ ምጣኔ ባለሁለት አሃዝ እድገት ማስመዝገብ ችሏል።

የኢትዮጵያ ዕድገት የጠንካራ ፖሊሲ ውጤት ነው። ምክንያቱም እስካሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ እዚህ ግባ የሚባል የተጥሮ ሃብት አላት የምትባል አገር አይደለችም። ይሁንና ኢትዮጵያ ላለፉት አስራ አራት ዓመታት ተከታታይና ፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ችላለች። አገራችን ይህን ፈጠን የኤኮኖሚ ዕደገት ለማስመዝገብ የቻለችው በተዓምር ሳይሆን መንግስት በተከተለው ትክክለኛ የኤኮኖሚ ፖሊሲ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። መንግስትን የሚመራው ገዥው ፓርቲ ነባራዊ ሁኔታውን በአግባብ ፈትሾ ሊተገበር የሚችልና ሁሉን የህብረተሰብ ክፍል አሳታፊ የሆነ እቅድ አዘጋጅቶ መተግበር በመቻሉ ነው። መንግስት እየተከተለ ያለው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር አገራችንን በሁሉም ዘርፎች ተጨባጭ ለውጥ እንድታስመዘግበ አግዟታል።

ልማታዊ መንግስት አመጣጡ በምስራቅ ኤዥያ ሲሆን ገዥው ፓርቲ የእነዚህን አገራት ተሞክሮ ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በመቀመር ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት መመስረት በመቻሉ አሁን እየታዩ ላሉ ለውጦችን መሰረት ሆኗል። ይህ መስምር ፍጹም ነው ወይም ምንም ችግር የለበትም ማለት ግን አይቻልም። ክፍተቶችና እጥረቶች ይስተዋላሉ። ይሁንና እነዚህ ክፍተቶችና እጥረቶች ሊታረሙ የሚችሉ እንደሆኑ ግን መካድ አይቻልም። ይህ መስመር አገራችንን ከቁልቁለት ጉዞ ታድጓታል። በሁሉም ዘርፍ በርካታ ለውጦችን ማስመዝገብ እንድትችል አድርጓታል። **ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አገራችንን ህገመንግስታዊ አገር እንድትሆን አስችሏታል።**

ኢትዮጵያ ህገ መንግስት አገሪቱን ከመበተን አደጋ ታግዷታል። የህዝቦችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ አድርጓል። የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን በመከተል ህዝቡ በየአምስት አመቱ በሚካሄድ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተወካዮቹን እንዲመርጥ አስችሎታል። በአገሪቱ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተጠብቀዋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ማንኛውም አካል የሃሳብ ልዩነቱን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማራመድ ይችላል። ለችግሮች በጠረጴዛ ዙሪያ መፍትሄ ማግኘት ለሚፈልግ አካል ሁኔታዎች የተመቻቹበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ የተረጋጋ ፖለቲካና ጠንካራ መንግስት አላቸው ከሚባሉ ጥቂት አገራት መካከል በቀዳሚነት የምትጠቀስ ሆናለች። ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ በጎረቤት አገራት ሰላም እንዲሰፍን የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ነች። ከዚህ ባሻገር የቀንዱ አካባቢ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍ የአካባቢው አገራት በኤኮኖሚ ጥቅም እንዲተሳሰሩ ለማድረግ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመተግበር ላይ ነች።

**ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አገራችንን ነጻ ወይም ገበያ መር የኤኮኖሚ ፖሊሲ እንዲኖራት አድርጓል።** ነጻ የኢኮኖሚ ስርዓትቱን በርካታ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ለግል ባለሃብቱ ክፍት እንዲሆኑ በመደረጉ ባለሃብቱ ትርፍ ያስገኙልኛል የሚላቸውን ዘርፎች በመለየት መሳተፍ የሚችልበት ሰፊ እድል እንዲፈጠር አድርገገል። በዚህም አገራችን ከፍተኛ እምርታ ማሳየት ችላለች።

በሌላ በኩል መንግስት ባለሃብቱ ሊሰማራባቸው በማይችሉ ወይም ትርፍ ሊያስገኙ በማይችሉ ዘርፎች ለአብነት ትላልቅ የሃይል ማመንጫዎች መገንባት፣ አውራ ጎዳናዎች ማስፋፋት፣ የባቡር ሃዲድ ዝርጋታዎች፣ የቴሌኮሙዩኒኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦት፣ የባቡር መስመር ዝርጋታ፣ ወዘተ በከፍተኛ ሁኔታ በማስፋፋት ላይ ይገኛል። ከዚህም ባሻገር ባለሃብቶች በተሰማሩባቸው ወይም ሊሰማሩባቸው በሚችሉ አካባቢዎች ሁሉ መንግስት የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን በተቻለ አቅም እያስፋፉ ይገኛል።

መንግስት ለትራንስፖርቱ ዘርፍ መዘመን ትኩረት በማድረጉ ከፍተኛ ካፒታል በመመደብ አገሪቱን ከወደብ ከተማ ማገናኘት የሚያስችል የባቡር መስመር ዝርጋታ ፕሮጀክት አካሂዷል። ሌሎች የባቡር መስመር ዝርጋታዎችም በመካሄድ ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ አየር መንገድም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በአለም በቀዳሚነት ከሚጠቀሱ አየር መንገዶች ተርታ መሰለፍ የቻለ ተቋም ነው። አየር መንገዱ ባሉት በርካታ መዳረሻዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለባለሃብቱ የካርጎ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህ የትራንስፖርት አማራጮች አገሪቱን የኢንቨስትመንት ተመራጭነት አሳድጎታል።

ሌላው የሃይል አቅርቦት ነው። ሃይል የሁሉም ነገር መሰረት ነው። መንግስት አገሪቱን የሃይል መዕከል ለማድረግ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በመገንባት ላይ ይገኛል። በመሆኑም አሁን ላይ የአገሪቱ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት በከፍተኛ ሁኔታ እድገት አሳይቷል። በቅርቡ እንኳን ጊቤ ሶስት የሃይል ማመንጫ በመመረቁ የአገሪቱን የሃይል አቅርቦት በእጥፍ አካባቢ አሳድጎታል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሃይል ማመንጨት ሲጀምር ደግሞ አሁን ያለው አቅርቦት ከእጥፍ በላይ ያድጋል። በዚያን ወቅት የአገራችን የሃይል አቅርቦት አስተማማኝ ያደርገዋል። በመሆኑም በቀጣይ ባለሃብቶች እንዲህ ያለ አስተማማኝ የሃይል አቅርቦት በተመጣጣኝ ክፍያ የሚያገኙ ከሆነ አገራችን የበርካታ ኢንቨስተሮችን ቀልብ መግዛቷ አይቀርም።

**ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አገራችን ፈጣን የማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንድትሆንም አድርጓታል።** የማህበራዊ አገልግሎቶችን ከማስፋፋት አኳያ መንግስት በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ። በትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ እድገት የታየበት ሲሆን የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ሽፋን በጥቅል ሲታይ ከ95 በመቶ በላይ ማድረስ ተችሏል። በከፍተኛ ትምህርት ረገድም በአገሪቱ በቀጣይ አምስት አመታት የሚገነቡትን አስር ዩኒቨርሲቲዎች ሳይጨምር እስካሁን ሰላሳ አምስት ዩኒቨርሲቲዎችን በፌዴራል መንግስት ብቻ መገንባት ተችሏል። ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ይገኛሉ።

በየዓመቱ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር ተማሪዎችን ማስመረቅ በመቻላቸው የአገሪቱን የሰለጠነ የሰው ሃይል ችግር ማቃለል ተችሏል። በተመሳሳይ በአገሪቱ ሁሉም ቀበሌዎች መሰረታዊ የጤና ባለሙያዎችን መመደበ በመቻሉ በጤናው ረገድ ስኬታማ ስራዎችን ማስመዝገብ ተችሏል። ከዚህ ቀደም አገሪቱ ትታወቅባቸው የነበሩ ተላላፊ በሽታዎችን በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ መግታት ተችሏል። በመከላከል ላይ መሰረት ያደረገው የአገሪቱ የጤና ፖሊሲ በስኬት እንዲታጀብ ሆኗል።

**ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አገራችንን የተረጋጋ ኤኮኖሚ እንዲኖራት አስችሏል።** የአገራችን ኤኮኖሚ የተረጋጋ በመሆኑ የዋጋ ግሽበት (ኢንፍሌሽን) ስጋት የለበትም። ከአምስት ዓመታት በፊት በአገራችን የዋጋ ንረቱ ወደ አርባ በመቶ ደረሶ የነበረ ቢሆንም መንግስት በተከተለው የማስተካከል እርምጃ በአጭር ጊዜ በአንድ ዲጂት እንዲገደብ አድርጎታል። የዋጋ ግሽበቱ በአንድ አሃዝ መገታት በመቻሉ አነስተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ከኑሮ ውድነት መታደግ ተችሏል። ባለሃብቶች በመንግስት ላይ እምነት እንዲኖራቸው ሆነዋል። ይህ ታላቅ ስኬት ነው።

ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አገራችንን ፈጣን የኤኮኖሚ እድገት እንድታስመዘግብ በማድረጉ የከተሞች እድገት በፍጥነት በማደግ ላይ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የከተሞች እድገት በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ ነው። የከተሞች እድገት ከህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ጉዳይ ነው። ከሃያ አመታት በፊት ከሃምሳ ሺህ በላይ የህዝብ ቁጥር የነበራቸው የአገራችን ከተሞች ብዛት በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። ይሁንና አሁን ላይ በአገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች ትላልቅ ከተሞች በመፈጠር ላይ ናቸው።

በከተሞች መስፋፋት ሳቢያ የመካከለኛ ገቢ ያለው የህብረተሰብ ክፍል በፍጥነት በማደግ ላይ በመሆኑ የህብረተሰቡ የተለያየ በተለይ እሴት የተጨመረባቸውን ነገሮች የመሸመት ፍላጎቱ እያደገ የመጣ እንደሆነ ማየት ይቻላል። ይህ የሚያመላክተው ለኢንዱስትሪ ውጤቶች አስትማማኝ የገበያ ዕድል በመፈጠር ላይ መሆኑን ነው። ግብርናን መሰረት ያደረገው የአገራችን ኤኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ የሚያደርገው ሽግግር ትክክለኛ መስመር ላይ መሆኑን ያሳያል።

መንግስት እየተከተለ ያለው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር አገራችንን ወደተሻለ ከፍታ በማውጣት ላይ ነው። ችግሮች የሉም ማለት አይቻልም። ይሁንና በአገራችን በመነጋገር ለችግሮች መፍትሄ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ተመቻችቷል። በመሆኑም ችግሮችን በሁከትና ብጥብጥ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ በሰከነና በሰለጠነ መንገድ መፍትሄ መፈለግ የመጀመሪያም የመጨረሻም አማራጭ ነው። ይህን በመድረግ አገራችን የጀመረችውን ዘርፈ በዙ ለውጥ ማስቀጠል የአገር ወዳድ ዜጋ ግዴታ ነው።